# እሹሩሩው አከተመ!!

# ተቃዋሚው፣ አሸባሪነትና አክራሪነት

***ኃይሉ ደመቀ***

07/14/14

አክራሪነትና አሸባሪነት በኢትዮጵያ የለም፤ አልተከሰተም የሚሉት ተቃዋሚዎችና ፅንፈኛው አክራሪ የፖለቲካ ኃይል ይህ ክህደታቸው ለፖለቲካዊ ድጋፍ ማሰባሰቢያ የሚጠቀሙበት ከመሆን አይዘልም፡፡ በዚህ ተግባራቸው ሕዝቡን እያዘናጉት ይገኛሉ፤ የሚገርመው ጥላቻቸው ወሰንየለሽ በመሆኑ አገርና ሕዝብ የሚለውን ትልቁን ቁም ነገር እስከመርሳት ደርሰዋል፡፡ ዴሞክራሲ ሠላምና ልዩነቶችን በሠላማዊ መንገድ መፍታት ነው፡፡ ዴሞክራሲ የትኛውንም ዓይነት የአስተሳሰብ ነፃነትና ልዩነት ማክበር፤ ከኃይል ውጭ በሠላማዊ መንገድ በውይይት ማስተናገድ ነው፤ ዴሞክራሲ የትኛውንም ዓይነት አሸባሪነትን ሆነ አክራሪነትንና ፅንፈኝነትን አይቀበልም፡፡ በየትኛውም አገር ተቀባይነት የለውምና፡፡

የተባበሩት መንግሥታት፤ የአውሮፖም ሆነ የአፍሪካ ህብረት ኃይማኖታዊም ሆነ ፖለቲካዊ አክራሪነትና አሸባሪነትን አይቀበሉትም፡፡ የተቃዋሚው ፖለቲካዊ አክራሪነት የመጨረሻው ግቡ አሸባሪነት ነው፡፡ የሚያመራውም ሆነ የሚሸጋገረው ወደ ጥፋትና እልቂት ምዕራፍ ይህም በአፍሪካና በሌሎችም የመካከለኛው ምሥራቅና የአውሮፖ አገሮች በተደጋጋሚ ታይቷል፡፡ ኃይማኖታዊ አክራሪነት ዛሬ በአፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ እንዲሁም በአፍጋኒስታንና በፓኪስታን ያለበትንና የደረሰበትን ደረጃ መመልከት ይበቃል፡፡ በዓለም ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ አሸባሪነትና አክራሪነት ዘግናኝና ሰቅጣጭ እልቂት እያስከተለና ይህም ድንበር የለሽ መሆኑን በአገራትም በአህጉራትም እንደማይወሰን እያየን ነው፡፡

የሶማሊያው አልሸባብ፤ የአፍጋኒስታኑ ታሊባን፤ ዓለም አቀፉ አሸባሪ አልቃይዳ፤ በኢራቅና በሶሪያ የሚንቀሳቀሰውና የካሊፋይት እስላማዊ መንግሥት እስከመመሥረት የደረሰው አይሲስ፤ የናይጄሪያው ቦካሀራም፤ የማሊው አንሣር ዲና በቂና ከበቂ በላይ ማሣያዎች ናቸው፡፡ አሸባሪነት ከኃይማኖታዊ ፖለቲካዊ አክራሪነትና የፅንፈኝነት አቋም ጋር በጽኑ የተቆራኘ መነሻውም ይኸው በመሆኑ በጅምላ እልቂት በደም መፋሰስና በአገር ሀብት መውደም አጥብቆ ያምናል፡፡ በዚህም ሂደት ተፈሪነትንና ተደማጭነትን እናገኛለን፤ ለድልም እንበቃለን የሚል ተስፋና እምነት አለው፡፡ ይህንን ለማሳካት በየአገራት የሚነሱ ብጥብጦችንና ሁከቶችን ይበልጥ በማቀጣጠልና በማስፋት ሥርዓተ አልበኝነት እንዲሰፍን ካደረገ በኋላ የተለያዩ ዘረፋዎችን በመፈፀም የጦር መሣሪያ አቅም በማግኘት የሰው ኃይል በብዛት በመመልመል ወደ ግልፅና ሰፊ ዘመቻ ይገባሉ፡፡ በቅርቡ በአለም የተለያዩ አገራት ሲሆን የታየውም ይኸው ነው፡፡

የእኛዎቹ ተቃዋሚዎች የሰለጠነ ተቃዋሚ በመሆን አግባብና ሕጋዊ በሆነ መልኩ ከገዥው ፖርቲ ጋር ያላቸውን የመርህ ልዩነትና ተቃውሞ ማሰማት በምርጫም በሕጋዊና ሠላማዊ መልኩ መሳተፍ ለአገራቸውም ለሕዝባቸውም ሠላም ትልቁና ወሣኙ ነጥብ መሆኑን ባይቀበሉትም ሊረዱት ግን ይገባል፡፡ በጥፋት፣ በጥላቻና ስሜታዊነት እየጋለቡ፤ በሕጋዊና ሠላማዊ መንገድ እንደሚሰሩ እየተናገሩ፤ ከጀርባ ደግሞ አሸባሪነትን ማራመድ፣ መደገፍ፣ አልፎ ተርፎም ከኃይማኖታዊ አክራሪ ኃይሎች ጋር ተሰልፎ ጥያቄያቸውን ማስተጋባት ርካሽ ድጋፍን ለማግኘት ሲሉ በረዥም ጊዜ የገንዘብና የሥልጠና ድጋፍ አድብቶ ቀን እየጠበቀ ካለ ፅንፈኛና አክራሪ ቡድን ጋር መቆምና አብሮ ማራገብ የአገርና የሕዝብ ክህደት ወንጀል ነው፡፡

ዓለም አቀፍ የደህንነትና የመረጃ ተቋማት በይፋ እንደገለፁት የዋሀቢና የሰለፊያ እስላማዊ አክራሪዎችን ለበርካታ አሥር ዓመታት በገንዘብ ፋይናንስ በማድረግ የተለያዩ የእስላማዊ አክራሪዎች ወታደራዊ ጅሀዲስቶች ማሰልጠኛ ጣቢያ በሚገኝባቸው አገሮች ሁሉ ወጪያቸውን እየሸፈነ እንዲሰለጥኑ ሲያደርጉ የኖሩትና ያሉት ሣውዲ ዐረቢያ፣ ኩዌትና ኳታር በሚሊዮኖችና በቢሊዬኖች የሚቆጠር ዶላር አፍስሰዋል፡፡ እነዚህ መንግሥታት ለሚቀርብባቸው ክስ ማስተባበያ ቢሰጡም ሣውዲ

ዐረቢ.ያ ብቻ በዓመት ሁለት ቢሊዬን ዶላር ድጋፍ ዋሀቢዝምን ለማስፋፋት ወጪ ማድረጓን በቅርቡ የቢ.ቢ.ሲ. ዘገባ አጋልጧል፡፡

በእነዚሁ አገራት የሚገኙ ቢሊዬነር አክራሪ እስላማዊ ከበርቴዎች ለዓለም አቀፍ እስላማዊ አሸባሪ ጅሀድ ቡድኖች እጅግ ከፍተኛው የፋይናንስ ምንጭ መሆናቸውንም የአገራት የመረጃ ተቋማት አረጋግጠዋል፡፡ በአንድ ወቅት ዊኪሊክስ ከአዲስ አበባው የአሜሪካ ኤምባሲ ወደ ዋሽንግተን የተላለፈውን የመረጃ ሰነድ በተጨባጭ ይፋ እንዳደረገው የዋሀቢ እስላማዊ አክራሪነት አደጋ በኢትዮጵያ ሥር ሰዷል፡ ፡ ገንዘቡም ኢትዮጵያ ውስጥ ይንቀሳቀሱ በነበሩት የሣዑዲ ዐረቢያ፣ የኩዌትና የኳታር መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት በሰፊው እንዲገባ ተደርጓል፤ በየቦታውም የመድረሣ ትምህርት ቤት አሰርተው ከውጪ ተምረው በመጡ ኢትዮጵያዊያን እስላማዊ አክራሪዎች አማካይነት በትምህርት ላልገፉ ወጣት ሙስሊሞች ይሰጣል፤ ለናሙና ያህልም ከደሴ እስከ መቀሌ ከተማ ባለው ርቀት እነዚሁ የኳታርና የኩዌት ዋሀቢና ስለፊስቶች ከ150 በላይ መስጊዶችን በጥንቱ የኢትዮጵያ መስጊድ አሠራር ሳይሆን በራሳቸው ሞዴል ሰርተዋል፤ ይህንን በተመለከተም ሰፊና ዝርዝር ተጨባጭ ማስረጃ ያለው ፅሁፍ ዊኪሊክስ አስነብቧል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛው ሙስሊሙ የሚኖርበትን አካባቢ ዒላማና የግባቸው መዳረሻ በማድረግ ወጣቱን ሙስሊም በአክራሪነት ለማጥመቅ ለመለወጥ በበርካታ ዓመታት ውስጥ በፀጥታና በዝምታ ሰርተዋል፡፡ ይህን የሚቃወሙ ሠላማዊና ተቻችሎ በመኖር የሚያምነውን የጥንቱን የኢትዮጵያ እስልምና እምነት የሚያራምዱ አባት ሼኾችን፣ አሊሞችንና ወልዮችን በመደብደብና በመግደል፤ የጥንት ሙስሊም መስጊዶችን በማቃጠል፤ ሕዝብ የሚያምንባቸውን የሼኾቹን መቃብሮች በማፍረስ የእምነት ሥፍራዎችን ለማውደም ሁሉ ተንቀሳቅሰዋል፡፡

በሕዝበ ሙስሊሙ ርብርብ የእነዚህ አክራሪ ሙስሊም ኃይሎች ሴራና ተንኮል ለጊዜው የከሸፈ ቢሆንም አሁንም ሥውሩ እንቅስቃሴያቸው እንደቀጠለ ነው፡፡ ከዚህ አልፈውም የጅሀድ ጦርነት የሚያራምድ ወታደራዊ ክንፍ "ካዋራጃ" የሚባል በመመሥረት ተንቀሳቅዋል፤ ቤተክርስቲያን አቃጥለዋል፤ ክርስቲያን ሙስሊም ሳይሉ በቆንጨራና በጥይት ገድለዋል፡፡ ይኸው በቤንሻንጉል ድንበር አካባቢ ይንቀሳቀስ የነበረው ኃይል ቢመታም ሴሉ በተለያዩ ቦታዎች ሊኖር እንደሚችል

ይታመናል፡፡ ከዓመት በፊት በከሚሴ አካባቢ መሣሪያ በመያዝ እሥር ቤት ሰብረውና ፖሊስ ገድለው የከተማዋን ስልክ መስመር በመበጣጠስ ለጊዜው ተሰውርው የነበሩና በኋላም በሕዝብና በፀጥታ ኃይሎች ትብብር የተያዙት፤ በደሴ ከተማም እስልምና ሠላም ነው፤ ፍቅር ነው፤ ተከባብሮ መኖር ነው፤ አክራሪነት አይበጀንም በማለት ሲያስተምሩ በነበሩትና ደጃፋቸው ላይ በጥይት ተደብደበው የወደቁት የ80 ዓመት አዛውንት ሞትስ የሚነግረን በአጠቃላይ አገሬ ሕዝቤ ለሚለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚያስተላልፈው ከባድ መልዕክትስ ምንድነው?

ከኢትዮጵያ መንግሥት አልፎ የምዕራቡ ዓለም ታዋቂ የመረጃ ተቋማት የእስልምና አክራሪዎች አደጋ በተጨባጭ በኢትዮጵያ ሥር እየሰደደ መሆኑን እየተናገሩ፤ አልሸባብ በኢትዮጵያ ላይ ተደጋጋሚ የጅሀድ ጦርነት ለአምስት ጊዜያት ያህል አያወጀ እየሰማን፤ የአሜሪካ ኤምባሲ በቅርቡ ጅሀዲስቶች የኢትዮጵያን ድንበር በተለያየ መልኩ እያቋረጡ ስለመግባታቸው መረጃ አለኝ፤ የአሜሪካ ዜጎች ተጠንቀቁ እያለ ባለበት በአገር ውስጥና በውጪ የሚገኙ ፅንፈኛ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ኃይሎች ከአክራሪ እስላማዊ ኃይሎች ጐን በመቆም እየደገፉ ይገኛሉ፡፡

ጥያቄቸው የመብት እንጂ የእስላማዊ አክራሪነት (እስላማዊ መንግሥት) በሂደት የመመሥረት ትግልና ጥያቄ አይደለም የሚሉበት ምስጢር በመንግሥት ላይ ካላቸው ፍፁም ጥላቻ የመነጨ እንጂ እውነቱ ጠፍቷቸው ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህም ለሚከተለው ጥፋትም ሆነ አደጋ እነሱም ሕዝቡን በማሳሳትና በማዘናጋት እየተጫወቱ ባለው የአገር ክህደት ቁማር ከአሸባሪዎቹ እኩል ተጠያቂ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እስላማዊ አክራሪት እና ፖለቲካዊ ጽንፈኝነት ፍፁም ፀረ ሠላም፣ ፀረ ዴሞክራሲ፣ ፀረ ልማት፣ ፀረ ሥልጣኔ፣ አረመኔያዊና ፋሽስታዊ ባሕርይ ያለው ነው፡፡

አሸባሪው እስላማዊ አክራሪ ኃይል በሶማሊያ፣ በኬንያ፣ በናይጄሪያ፣ በማሊ፣ በኢራቅ፣ በሶሪያ፣ በግብፅ፣ በሊቢያ፣ በፖኪስታን፣ በአፍጋኒስታን በተግባር በታዩት ተጨባጭ ድርጊቶቹ ከራሱ እምነት ውጪ ለቆመ ለየትኛውም ግለሰብ፣ ሕዝብ፣ መንግሥት አንድም ምንም ዓይነት ምህረትና ርህራሄ የለውም፡፡ ይህ ዓይነቱን አደጋ አስቀድሞ ለመከላከል ገና መሠረት ሳይጥል ለመንቀል መንግሥት ለሕዝቡ በማሳወቅ

እየተረባረበ ባለበት ወቅት ተቃዋሚው የፖለቲካ ኃይል በእዚህ ራሱን ሕዝቡን አገሪቱን በሚመለከት እጅግ አሳሳቢ አደጋና የህልውና ጉዳይ ላይ ከሕዝብና ከመንግሥት ጐን ቆሞ በቁርጠኝነት መከላከል ይገባው ነበር፡፡

ለአባላቱም ስለ እስላማዊ አክራሪነት የከፋ አደጋ ማሳወቅና ማስተማር አገራችንን ዒላማ ካደረጉ መቆየታቸውን ማሳወቅ ቀዳሚ ድርሻው ባደረገ ነበር፡፡ ኢሕአዴግን ስለሚቃወም ብቻ የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው በሚል ሙት መፈክር ጭራሹንም አገሪቷንና ታሪኳን የማንነት መሠረቷንም ሊያወድም፤ ለረዥም ዘመናት ሲያደባና ውስጥ ውስጡን ሲደራጅ ኖሮ ተቃውሞውን በሽፋን በመብት ስም አደባባይ ካወጣው የዋህቢና የሰለፊያ እስላማዊ አክራሪ ኃይል ጐን መቆምና መሰለፍ የከፋው የአገር ጠላትነት መገለጫ መሆኑን ዛሬም ነገም ሊያውቀው ይገባል፡፡ አገርና ሕዝብ በየትውልዱ ፈረቃ ቋሚ ሆነው ይቀጥላሉ፡፡ መንግሥታት ሊለዋወጡ ይችላሉ፡፡ የአገርና የሕዝብ ደህንነት ፀጥታና ሉዓላዊነት ሁሌም ቀዳሚና ለድርድርና ለውይይት የሚቀርብ አጀንዳ አይደለም፡፡ ተቃዋሚው ከአሸባሪዎች ጐን በመቆሙ የአገርና የሕዝቡን ሠላም ፀጥታ ደህንነትና ሉዓላዊነትን አሳልፎ መስጠቱ እንደሆነም አያከራክርም፡፡ ድጋፍ ከመስጠት አልፎ አሸባሪነትና አክራሪነት ለኢትዮጵያ ታላቅ አደጋ መሆኑን በማመን አቋሙን አልገለፀም፡፡

ሰሞኑን የግብጹ ፕሬዚዳንት ፊልድ ማርሻል ሲሲ "በየመስጊዱ መሽገውና በየጁምዓው ፀሎት የሚያሴሩትና የሚጮሁት ለአገራችን ሠላምና ፀጥታ አደጋ መሆናቸውን የአገሪቱ ሕዝብ ሊያውቅና አገርን ሊጠብቅ ይገባል፡፡ በኃይማኖት አክራሪነት ምክንያት ብዙ አገራት ፈራርሰዋል፤ ይህንንም አይታችኋል ብለዋል፡፡ ምክንያቱም የዓረቡ ዓለም በርካታ አገራት የነበራቸው ክብር፣ ሠላም፣ መረጋጋት፣ የሕዝባቸው ሕይወት፣ የአገራቸው ሀብት ወድሞና ብትንትኑ ወጥቶ በታሪክ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ ፈራርሰዋል፡፡

የተለያዩ ጅሀዳዊ አሸባሪ ኃይሎች መሣሪያ ታጥቀው እርስ በእርስ የሚፋለሙበት፤ ሥርዓት አልበኝነት የነገሰበት፤ ወጥቶ መግባት ያልተቻለበት ምክንያቱ መንግሥታት በመፈራረሳቸው ነው፡፡ የዚህም መነሻው የዓረቡ አለም የቀለምና በሌላው ጎኑ በአክራሪ እስላማዊ ኃይሎች የተመራው አብዮት ነው፡፡ በኢራቅና ሶሪያ ሰሞኑን የካሊፋይት እስላማዊ መንግሥት መመሥረቱን ይፋ ያደረገው አይሲ

በዓለም ከበርቴው የአሸባሪ ድርጅት ተብሎ ሲሰየም እስከ አንድ በሊዬን ዶላር የሚደርስ ካፒታል አለው፡፡ ከኢራቅ ሠራዊት ከማረከው የአሜሪካና የሩሲያ ታንኮች፣ መድፎችና ዘመናዊ መሣሪያዎች ሌላ ይስራ አይስራ ባይታወቅም ሚሳኤል በእጅ እንዳስገባ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች አሳይተዋል፡፡ ሕገ ወጥ ወንብድና፣ ዝርፊያ፣ ነጠቃ፣ ሀብታሞችን ማፈን፣ በቅርቡ ሞሱል ከተማ ላይ ባንክ ዘርፎ ካገኘው 430 ሚሊዮን ዶላር ሌላ በተቆጣጠራቸው አካባቢዎች ከሚገኙ የነዳጅ ዘይት ጉድጓዶች ነዳጅ እያወጣ የኤሌክትሪክ መስመርም በዶላር በመሸጥ አቅሙን ገንብቷል፡፡

አክራሪ እስልምናን በሚያራምዱ የተለያዩ ምሁራን፣ ወታደራዊ አዋቂዎች ጭምር የተገነባ ከዚህ በፊት ያልተለመዱ ሥልቶችን ጭምር የሚጠቀም መሆኑ በሰፊው ተዘግቦለታል፡፡ ለወትሮው ፈጣን ምላሽ የሚሰጡት ምዕራባውያን በተለይም እንግሊዝና አሜሪካ ሁኔታውን ከማጥናትና ከመከታተል ባለፈ ክፉኛ በመደናገጣቸው እርምጃ ለመውሰድ አልደፈሩም፡፡ ይህ አደጋ ከመካከለኛው ምሥራቅ አልፎም ከአልቃይዳ ጋር የተሳሰረ ታላቅ ዓለም አቀፍ አደጋን በተለይ እስላማዊ አክራሪነትን በማዛመት እንደሚያመጣ ዓለም አቀፍ የደህንነት ኤክስፐርቶች፤ በአሸባሪነትና በአክራሪነት ላይ ጥልቀት ያለው ጥናትና ምርምር ያደረጉ የኃይማኖት፣ የታሪክ፣ የፖለቲካ ሣይንስ፣ የግጭት ባለሙያዎች በስፋት እየተናገሩ ይገኛሉ፡፡

ለእኛ አጐራባች የሆነውም የሶማሊያው አልሸባብና አልቃይዳም በኢትዮጵያ ሊዘረጉት የሞከሩት የአልቃይዳ ሴል መኖሩ ተደርሶበታል፤ ከእነዚህ ኃይሎች ጋር እጅና ጓንት ሆነው በመሥራት ተሞክሮ በመውሰድ ባይሳካላቸውም ለመንቀሳቀስ መሞከራቸው አይቀርም፡፡ ይህን ሁሉ ጠንቅቆ የሚያውቀው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይል ይኼ በአገሪቷ ላይ የተደቀነ እጅግ አደገኛ የብሔራዊ ሕልውና ጥያቄ አያሳስበውም፡፡ ይልቁንም በአወሊያ ትምህርት ቤት የዋሀቢያዎች መናኽሪያነትና ጐራ ምክንያት የተቀሰቀሰ እየተጋጋመ በመሄድ ኮሚቴ እስከማዋቀር የደረሰው አካል የሙስሊሙ ወኪል የተባለውና እነ ድምፃችን ይሰማ የሚለው የአክራሪ ሙስሊሞች ስብስብ ከጀርባው በማን ይረዳል፤ ዓላማውስ ምንድነው፤ ለምንስ በተቃውሞው ገፋበት፤ ለምንስ የዓረቡ ዓለም ሚዲያ ጉዳዩን እየተከታተለ ከአገር

ውስጡ ቅጥረኛ አንዳንድ የግሉ ሚዲያና ከነኢማት ጋር በመተባበር ማጧጧፉን ተያያዘው? ብሎ ለመመርመር አልፈቀደም፡፡ ተቃዋሚው ኢሕአዴግን ስለሚጠላ ብቻ ከአገርና ከሕዝብ ጠላቶች ጋር ሲፈልግም ከአልሸባብና አልቃይዳ ጋርም ተባብሮ ለመቆም ወስኗል፡፡ እጅግ አሳዛኝ፤ እጅግ አሳፋሪ፤ የአገርና የሕዝብ ክህደት ወንጀል ነው፡፡ አወሊያ ትምህርት ቤት ለረዥም ዘመናት በእርዳታ ሲተዳደር የነበረው በሣዑዲ ዐረቢያ፣ በኩዌትና በኳታር የዶላር እርዳታ ነበር፡፡ ጉዳዩ ተደርሶበት እርምጃ ከመወሰዱ በፊት በደርግም ዘመን ቢሆን ስላላመቻቸው አልተንቀሳቀሱም እንጂ የአክራሪነት አስተምህሮን በወጣቱ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ዘንድ ውስጥ ለውስጥ ሲያሰርጹ ኖረዋል፡፡

አወሊያ ትምህርት ቤት ከዓረቡ ዓለም የሚፈሰው ገንዘብ ከትምህርት ቤቱ አስፈላጊ ወጪ ውጪ ኢትዮጵያ ውስጥ ምን ሲሰራበት እንደኖረ፤ ለአክራሪ ዋሀቢ ግለሰቦች እየተሰጠ እምነቱን ለማስፋፋትና የገንዘብ አቅማቸውን ለማጎልበት ምን ምን ድርጅት እንደከፈቱበት፤ በተለያዩ መስኮች ምን ዓይነት የገንዘብ ማግኚያ ድርጅቶችና ተቋማት፣ መደብሮች፣ ሆቴሎች፣ ሱፐር ማርኬቶች፣ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጫዎች፣ ፋብሪካዎች፣ ህንጻዎች ወዘተ እንደተገነቡና እንደተቋቋሙ፤ በግለሰብ ሀብት ስም ተመዝግበው በሥውር ለምን ዓላማ እንደሚውሉ፤ በክልሎችና በተለያዩ ከተሞችስ ይህ በሽፋን እየገባ ለሥውርና ድብቅ የኃይማኖታዊ ፖለቲካዊ ሥራ የሚውል ገንዘብ ሥርጭቱና ተፋሰሱ እስከ የት ድረስ እንደሆነ መንግሥት በከፊል ምስጢሩን ከደረሰበት በኋላ በስፋት እየተከታተለው እንደሚሆን ይገመታል፡፡ ጉዳዩ የአገርና የሕዝብ ሕልውና ከባድ ጉዳይ ነውና፡፡ ኢኮኖሚውንም በበላይነት ለመቆጣጠር የተሄደበት ርቀት ራሱን የቻለ ጉዞ መሆኑንም ማስተዋል ይገባል፡፡

ኮሽ ሳይል መንግሥትም ሕዝብም ሳይነቃ ለረዥም ጊዜ የሄዱበት መንገድ አክራሪ የዋሀቢና ሰለፊያ አስተምህሮትን በኢትዮጵያ የተለያዩ ክልሎች በማስፋፋት የወጣቱን ሙስሊም አካላዊና አዕምሮአዊ ብቃቱ እየጐለበቱ፤ በገንዘባቸው በስሙ ድርጅት እንዲከፍት በማድረግ ከሌላው ኅብረተሰብም የተሻለ የኢኮኖሚ አቅም እንዲገነቡ በተለይም ለመንግሥት ደጋፊ ሆኖ በመቅረብ ከጥርጣሬ እንዲያወጣቸው የማድረግ ሥልትን ተጠቅመዋል፡፡ አዛውንቶቹን አባት ሙስሊሞች አክርረው

የሚቃወሟቸው ድርጊታቸውን ስለሚያውቁና ስለሚያወግዙት ነው፤ አብዛኛው ወጣት ሙስሊም የተጠለፈበት ምስጢርም ይኸው ነው፡፡

በርካታ ወጣት ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ለሥራና ለሀጂ በሚል ሳውዲ ዐረቢያ በመሄድ ብዙ ዓመታት እየሰሩም አክራሪ ዋሀቢነትን እየተማሩ ኖረዋል፡፡ የግብጹ ሙስሊም ብራዘር ሁድ ከንጉሱ ጊዜ ጀምሮ በደርግም፣ በኢሕአዴግም በተለያየ ሽፋን በነፃ የትምህርት እድል ወጣት ሙስሊም ኢትዮጵያውያን እንዲያገኙ እያደረገ ፅንፈኝነትን አስተምሯል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥም ከንጉሱ ጊዜ ጀምሮ አባላት እንዳሉት ይታመናል፡፡

በሱዳን ካይሮ አክራሪው እስላማዊ መሪ ዶክተር ሐሰን አልቱራቢ በሱዳን መንግሥት አመራር ላይ በነበረበት ወቅት ሳይታገድ በፊት ያ ጊዜ ቢንላደንም ሱዳን የነበረበት ስለነበረ ለወጣት ሙስሊም ኢትዮጵያውያን በገፍ የነፃ የሀትምህርት እድል በመስጠት በእስላማዊ ኮሌጅና ዩኒቨርስቲዎች ሠላማዊውን እስልምና ሳይሆን አክራሪውን የእስልምና እምነት ለአራትና አምስት ዓመታት እየተማሩ ተመልሰዋል፡፡ በ1987 አካባቢ በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት አመራር ምርጫና ቦታ ድልድል ላይ ተከስቶ የነበረውና በኋላም ታላቅ ሠላማዊ ሰልፍ እስከ ማድረግ የተሄደበት ረዥም ጉዞ እነዚሁ ፅንፈኛ ኃይሎች ውስጥ ለውስጥ በፀጥታ ያደረጉት የቅስቀሳ ውጤትና በኃይል ማግያነትም የተጠቀሙበት ነበር፡፡ በኋላም ግጭቱ በሽምግልና አልቀጭ ብሎ እስከ ግጭት፣ አመፅና ሁከት፣ ደም መፋሰስ፣ ንብረት መውደም ደርሶ መንግሥት ጣልቃ በመግባት ጉዳዩን በማብረድ ታስረው ጉዳዩ ለረዥም ጊዜ በፍርድ ቤት ሲታይ እንደነበረና እንደተቋጨ ይታወቃል፡፡

ያኔም የግጭቱ ማዕከላዊ ነጥብ የዋሀቢያና የሰለፊያ አክራሪ ሙስሊሞች ሕጋዊውን የኢትዮጵያ እስልምና ጉባዔ ጠቅላይ ምክር ቤት በገንዘብ ኃይል ደጋፊን በማብዛት አመራሩን በመቆጣጠር፤ በሕጋዊው ሽፋን በአዲስ አበባና በክልሎች ያለውን የምክር ቤቱን መዋቅር በመጠቀም በመላው አገሪቱ የዋሀቢንና የሰለፊያን እስላማዊ አክራሪነት ለማስፋፋት የነበራቸው ተስፋ በእውነተኞቹ ሠላማዊ የጥንቱን

የኢትዮጵያ እስልምና እምነት አክብረው በሚከተሉት አባቶች ሼኼች፣ አሊሞች፣ ወሊዮች፣ ታላቅ ትግል በመክሸፉ ነው፡፡ አባቶች እስከዚህ ድረስ ለአገራቸውና ለሕዝባቸው ሠላምና አንድነት ሲሉ ታላቅ ተጋድሎ አድርገዋል፡፡

የፖለቲካ ተቃዋሚ ነኝ፤ አገሬ ሕዝቤ እያለ የሚፏልለው ስመ ብዙ መንጋ ግን ኢሕአዴግን ከማጥላላት ውጪ ከእንዲህ ዓይነቱ ታላቅ የአክራሪዎች ጥንስስ ሴራና አደጋ ባለው አቅም አገሩንና ሕዝቡና መከላከልና ነቅቶ እንዲጠብቅ አላሳወቀውም፡፡ ጭርሱንም አብሮ እያዳለቀ፣ እያጫፈረና በርቱ እያለ ይገኛል፡፡ እንዲህ ዓይነት አሳፋሪና ማፈሪያ የሆኑ ተቃዋሚዎች ናቸው ያሉን፤ መቼም አንዴ እብደት ውስጥ ናቸውና እነሱም አብረው እስላማዊ መንግሥት ለመመሥረት ተዋውለው ይሆን እንዴ ተብሎ ቢጠረጠር አያስገርምም?

በቅርቡ አወልያ ትምህርት ቤት በእስልምና ጠቅላይ ምክር ቤት ሥር እንዲሆን በመደረጉ ታላቁ የአክራሪዎች የገንዘብ ምንጭ እንደሚነጥፍ ሲረዱ በሁለተኛም ደረጃ ሕዝበ ሙስሊሙ በአዲስ አበባና በክልሎች በነቂስ ወጥቶ በያለበት ቀበሌና ወረዳ ምርጫ በማድረግ አመራሮቹን ከአክራሪ ሙስሊሞች በማፅዳት በመምረጡ ክፉኛ የተበሳጩት የዋሀቢያና የሰለፊያ አክራሪ ሙስሊሞች ለዓላማቸው መሳካት የማፈልጉትን ቁልፍ ቦታ ስላጡት ምርጫው ሕጋዊ አይደለም፤ መካሄድ የነበረበት በየመስጊዱ እንጂ በቀበሌ፤ በየወረዳው አይደለም፤ መንግሥት ጣልቃ ገብቷል፤ ምርጫውን አንቀበልም፤ የታሰሩት ይፈቱ ወዘተ ጩኸቶች በማሰማት ይህንንም በዓርብ ጁምዓ ፀሎት በማካሄድ፤ በፌስ ቡክ (ድምጻችን ይሰማ) ፔጅ እንዲሁም በሞባይል መልዕክት በየወቅቱ በማስተላለፍ፤ እቅድና አፈፃፀም የትግል ሥልት የሚሉትን በዝርዝር በማቀድና በመግለጽ፤ በማስተባበርና በማሰራጨት ልክ እንደ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ በመሆን ደግሞም አዎ ኃይማኖታዊ የፖለቲካ አክራሪ ድርጅት ናቸውና ሠላማዊ ነን ቢሉም ለሁከትና አመጽ ተንቀሳቅሰዋል፡፡ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት እየሰሩም ነው፤ አይዟችሁ ባዩቹ ደግሞ እነ ሰማያዊ ፓርቲ፣ ግንቦት ሰባትና ሌሎችም ናቸው፡፤

የዋሀቢያና የሰለፊያ እስላማዊ አክራሪ ኃይሎች ወጣቱን ሙስሊም በመቀስቀስ ወረቀት በመበተን፤ ለኃይማኖታዊ ጅሀድ ለዲንህ (ለኃይማኖትህ) ለመሞት ተነስ፤ አምፅ፤ ብትሞትም ነፍስህ ለጀነት (ገነት) ነው እያሉት ነው፤ ከተቃዋሚ ፖለቲካ ፖርቲዎችም ጋር በአገር ውስጥም በውጭም እጅና ጓንት ሆነው አብረው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

አብዛኛውና ጨዋው ተከባብሮና ተቻችሎ በመኖር የአገሩን ሠላም፣ ልማትና እድገት የሚመኘው ኢትዮጵያዊ ሙስሊም በአዲስ አበባና በክልሎችም ከእነዚህ አክራሪ የሙስሊም ኃይሎች ጋር ከፍተኛ ትንቅንቅ እያደረገ፣ እየታገላቸው፣ እያጋለጣቸውም ይገኛል፡፡

ኃይማኖታዊም ሆነ ፖለቲካዊ አሸባሪነትና አክራሪነት ለኢትዮጵያ መቼም አይበጃትም፡፡ የአሸባሪነትም ሆነ የፖለቲካ አክራሪነትና ፅንፈኛነት የመጨረሻው ግብ ፀረ ሠላም፤ ፀረ ልማት፤ ፀረ ዴሞክራሲ በመሆኑ ደም መፋሰስና እልቂትን ያስከትላል፡፡ አስቀድመን ልንከላከለው ይገባል፡፡ አራምባና ቆቦ እየረገጠ በጥላቻና በስሜታዊነት እየተቆላ የሚርገፈገፈው፤ በሠላማዊነት ስም ተሸፍኖ የሚያሴረው ተቃዋሚ ኃይል ግልፅ አቋሙን ለሕዝብ ማሳወቅ አለበት፡፡

ኢትዮጵያን ከአሸባሪና እስላማዊ አክራሪ ኃይሎች አደጋ መታደግ ወይንም የእነሱን መንገድ መርጦ ለይቶለት ጅሀድ ብሎ መቆሙን ይግለጽ፡፡ ይኼኔም አገርና ሕዝብ የማያወላዳ ቁርጥ ያለ ውሣኔ ይሰጣሉ፡፡ ኢትዮጵያን ከማንኛውም የአሸባሪነትና የአክራሪነት አደጋ ለመከላከልና ለመጠበቅ ሕዝቡ በአራቱም ማዕዘናት ለሊትም ቀንም ከመንግሥት ጋር ዘብ ይቆማል፡፡ የእሹሩሩው ጊዜውም አከተመ፡፡